Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY
PUBLIC SCHOOLS

# ለ4ኛ ክፍል ተማሪዎች ዓመት የሚወስድ የዳበረ የማንበብ እና መጻፍ ካሪኩለም (ELC) ትምህርት የወላጅ መመሪያ

ተማሪዎች በ4ኛ ክፍል እያሉ፣ ከዚህ በታች በተገለጹት ጽንሰሃሳቦች እና ክህሎቶች ላይ ትምህርት ያገኛሉ።

## ELC ንባብ

| 1ኛ የማርክ መስጫ ወቅት | 2ኛ የማርክ መስጫ ወቅት |
|---|---|
| ተማሪዎች በርካታ የተመረጡ የJunior Great Books Series 4 ስነጽሑፍ እና Nonfiction Inquiry ጽሑፍ በማንበብ የጥንካሬን ዘዉግ በመቃኘት ጠንካራ ይሆናሉ። የቅርበት ንባብ፣የተጋራ ጥያቄን መጠቀም፣ እና በተቀጽላ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍ ተማሪዎች እንዲመረምሩ፣ እንዲያብላሉ/እንዲያዋሂዱ፣ እና በጥልቀት እንዲረዱ ይረዳቸዋል።<br><br>አደረጃጀት እና የጽሑፍ መዋቅሮችን፣ የጽሑፍ ባህሪያትን፣ ጎራ-ተኮር ቃላትን ለመለየት፣ እና የመረጃ መጽሐፍን ለማዳበር እንዴት በብቃት እና በዉጤታማነት ማስታወሻዎችን ለመውሰድ እንዲችሉ ተማሪዎች በማህበራዊ ጥናቶች እና በሳይንስ ውስጥ ያሉ የጥናት ርዕሶችን የሚመለከቱ የመረጃ ጽሑፎችን ያነባሉ። የተማሪዎችን ወሳኝ እና የፈጠራ አስተሳሰብ ችሎታቸውን ለማዳበር እና ለማጥራት የውይይት ሞዴሎች፣ የተለዩ የማስተማር ስልቶች፣ እና መልቲሚዲያ ፅሁፎች ጥቅም ላይ ይዉላሉ። | ተማሪዎች በርካታ የተመረጡ የJunior Great Books Series 4 ስነጽሑፍ እና ሁለት Nonfiction Inquiry ጽሑፍ በማንበብ የኮሚኒኬሽን/ግንኙነት ጭብጥን ይመረምራሉ። ስለ ጽሑፉ እና ከግንኙነት ጽንሰሀሳብ ጋር ስላለዉ ግንኙነት ያላቸውን ግንዛቤ ለማጠንከር እና ጥልቅ ለማድረግ ተማሪዎች ከእያንዳንዱ ምርጫ በኋላ በተቀጥያ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ይሳተፋሉ።<br><br>መረጃዊ ጽሑፎቹ ከሳይንስ ትምህርት የአካባቢያዊ ጥናቶችን ርዕስ እና በማህበራዊ ጥናቶች ውስጥ ኢኮኖሚክስን፣ እንዲሁም የሰዎች እንቅስቃሴ በሜሪላንድ ኢኮኖሚ ላይ ያለዉን ተጽእኖ ያጣምራል። የመጀመሪያ እና የሁለተኛ-እጅ ድርሳን የጋዜጠኝነት አፃፃፍ ልምድን ለመደገፍ በርእሰአንቀጽ፣ አርእስቶች፣ ድርጅታዊ መዋቅሮች፣ድምጸት/ቃና፣ እና በመደምደሚያ ግምቶች ላይ ካተኮሩ ከበርካታ የተለያዩ የዜና ታሪክ ጋር ይነበባሉ። |
| **3ኛ የማርክ መስጫ ወቅት** | **4ኛ የማርክ መስጫ ወቅት** |
| ተማሪዎች የ William and Mary Autobiographies and Memoirs English Language Arts Unit/የዊሊያም እና ሜሪ በራስ የተጻፈ ታሪክ እና ትዉስታዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ኪነጥበባት ክፍል ሙሉ ትግበራ ላይ ይሳተፋሉ። ተማሪዎች ልብ ወለድ እና ልቦለድ ያልሆኑ የፅሁፎች ስብስብ በማንበብ ምላሽ መስጠት እና ጽሑፎችን ለመተንተን፣ ቁልፍ ቃላቶችን ለመመርመር፣ ሂሳዊ የአስተሳሰብ ችሎታዎችን ለማዳበር፣ እና የአጭር እና የረጅም ጊዜ ዉጤቶችን ለመፃፍ በተለዩ የማስተማር ሞዴሎች ውስጥ ይሳተፋሉ። ተማሪዎች ስለ ራስ በራስ የተጻፈ ታሪክ/አዉቶባዮግራፊያዊ ሥነ-ጽሑፎችን በማንበብ እና ልበወለዶችን፣ አጫጭር ታሪኮችን፣ ቅኔዎችን፣ የሥነጥበብ ስራዎችን፣ እና ሙዚቃን በጥልቀት በማጥናት የተለያዩ ደራሲያንን ይመረምራሉ።<br><br>በዊልያም እና ሜሪ ዩኒት/ክፍል ውስጥ የደራሲያን ስራዎችን የበለጠ ለመተንተን እንዲሁም ለቅርበት የንባብ ሂደት ልዩ ትኩረት ለመስጠት ሶስት የ Junior Great መጽሐፍት ምርጫዎች ይነበባሉ። የመረጃ ፅሁፎች ትምህርቶች በካልኪንስ ዩኒት/ክፍል ውስጥ ያለውን ሥራ የሚደግፉ እና በዊልያም እና በሜሪ ዩኒት/ክፍል ውስጥ የምርምር ፕሮጀክትን ፊትለፊት ያቀርባሉ። | ተማሪዎች የ William and Mary Autobiographies and Memoirs English Language Arts Unit/የዊሊያም እና ሜሪ በራስ የተጻፈ ታሪክ እና ትዉስታዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ኪነጥበባት ክፍል ሙሉ ትግበራ ላይ ይሳተፋሉ። ተማሪዎች አጫጭር ታሪኮችን እና ግጥሞችን ያነባሉ፣ እንዲሁም የቃላት ቁብ/ድር፣ የሥነጽሁፍ ቁብ/ድር ያጠናቅቃሉ፣ እናም ለንባብ ምላሽ ለመስጠት አጫጭር ታሪኮችን ይጽፋሉ። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች እራሳቸው የሚመርጡት የደራሲያን ልብ ወለድ ሥራዎችን ማንበብ ያጠናቅቃሉ።<br><br>ለጉዳይ-ተኮር ምርምር እና እንደ የመረጃዊ መጽሐፍ/ፎች ጥንቅር አካል የሆነ ታሪካዊ ልብ ወለድ ለመጻፍ የሚስፈልጉትን ክህሎቶች ወደፊት ለማምጣት ተማሪዎች ከስነጽሑፍ ምርጫ ጋር የተጣመረ ልብ-ወለድ ያልሆኑ Junior Great Books ያነባሉ። ተማሪዎች ታሪካዊ ልብ ወለዶችን፣የምርምር ንዑስ አርእስቶችን የሚያነቡ ሲሆን፣ እንዲሁም ፅሁፍን ለመደገፍ በአነስተኛ ቡድን ትምህርት እና በግል ጥናት ሲያደርጉ ማስታወሻ ይይዛሉ። |

## ELC መጻፍ

| 1ኛ የማርክ መስጫ ወቅት | 2ኛ የማርክ መስጫ ወቅት |
|---|---|

© 2019 ፈጣንና የዳበረ ትምህርት

| | |
|---|---|
| ተማሪዎች በየእለቱ ጽሑፍ የሚለማመዱ ሲሆን በሙሉዉ የዩኒቱ/ክፍሉ ጊዜ ሁሉ ሲጠየቁ በመፃፍ እና ለንባብ ምላሽ ለመስጠት በሚደረግ ጽሑፍ ላይ ይሳተፋሉ።<br><br>የክፍሉን/ዩኒቱን ጭብጥ ግንዛቤ ለማዳበር ተማሪዎች የግል ትረካ በማዘጋጀት በጽሑፉ ሂደት ውስጥ ይሳተፋሉ። የጽሑፍ ትረካ ችሎታ በሉሲ ካልኪንስ ዩኒት/ክፍል 1 በጽሑፍ ውስጥ በተጨማሪ ይዳብራል፦The Arc of Story። ተማሪዎች ለክዋኔዉ እድገት/መቀጠል እንዲያግዝ በገጸባህሪ አስተሳሰብ፣ ተግባር እና ውይይቶች አማካይነት ስለ ገጸባሕሪ ብየና ይማራሉ።<br><br>በማርክ መስጫዉ ጊዜ ሁሉ የተራዘመ የጽሑፍ ፕሮጀክቶችን ለመለማመድ እድሎችም አሉ። | ዩኒት/ክፍል 2፣ Boxes and Bullets፣ በጽሑፍ የካልኪንስ ዩኑት/ክፍል፣ ተማሪዎችን የግል እና አሳማኝ መጣጥፎችን በ ፈጣን-ረቂቅ እንዲጽፉ፣ የድርሰት መግለጫዎችን ማዘጋጀት፣ ማስረጃዎችን መሰብሰብ እና ማደራጀት፣ ጠንካራ መግቢያዎችን እና ድምዳሜዎችን ማዘጋጀት፣ እና በራስ አመለካከት ግልፅነትን እንዲገመግሙ ያስተምራቸዋል።<br><br>በዩኒቱ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች በጋዜጠኝነት ዘርፍ ወደ አጭር ክፍል/ዩኒት ይሄዳሉ/ይዞራሉ እናም አነስተኛ ጋዜጣ ወይም የዜና አውታር ለማዘጋጀት ይሰራሉ። |
| **3ኛ የማርክ መስጫ ወቅት** | **4ኛ የማርክ መስጫ ወቅት** |
| ተማሪዎች የ William and Mary Autobiographies and Memoirs English Language Arts Unit/የዊሊያም እና ሜሪ በራስ የተጻፈ ታሪክ እና ትዉስታዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ኪነጥበባት ክፍል ሙሉ ትግበራ ላይ በመሳተፍእና በራስ የተጻፈ የራስ ታሪክ እና በቃል ማቅረብን ያዘጋጃሉ።<br><br>ተማሪዎች ስለ ስምንት የንግግር ክፍሎች የሚማሩበት እና ባልታወቁ ወይም ባልተለመዱ ቃላት ላይ ለመተግበር እና አዲስ ዕውቀት በራሳቸው ጽሑፍ ላይ ለመተግበር እንዴት የግሪክ እና የላቲን ሥረ-ቃላትን እንደሚተነትኑ የሚማሩበት የሰዋሰዉ ጥናት በዩኒቱ/ክፍሉ ዉስጥ ተካቷል።<br><br>በጽሑፍ የካልኪንስ ዩኒት/ክፍል ጥናት፣የማንበብ እና መጻፍ መጣጥፎች ከአስተያየት መጣጥፎች ወደ መረጃ ሰጭ/ገላጭ መጣጥፎች እንዴት መሸጋገር እንደሚቻል ላይ የሚያተኩር፣ እና የጽሑፍ አወቃቀርን ማወዳደር/ማነጻጸርን ያጎላል። | ተማሪዎች በጉዳይ ላይ የተመሰረቱ ጽሑፎችን ለመገምገም የአስተሳሰብ ክፍሎች/ኤለመንትስ እና የአስተሳሰብ መመዘኛዎችን ይማራሉ። ተማሪዎች እነዚህን ችሎታዎች በመጠቀም፣ በመረጡት ርዕስ ላይ ሪፖርት እና የቃል አቀራረብ ለማዘጋጀት በዊሊያም እና በሜሪ የምርምር ሞዴል ውስጥ ይሳተፋሉ።<br><br>ተማሪዎች የዊሊያም እና ሜሪን ዩኒት የሚያጠቃልሉት በ Autobiographies and Memoirs English Language Arts Unit ዉስጥ በሙሉ አሳማኝ መጣጥፎችን በመጻፍ እና በእድገታቸው እና በትምህርታቸው ላይ በማነጣጠር ድህረ ግምገማ በማጠናቀቅ ነዉ።<br><br>ተማሪዎች በጽሑፍ የመጨረሻዉ የካልኪንስ ዩኒት/ክፍል ውስጥ ይሳተፋሉ፦ታሪክን ወደ ሕይወት ማምጣትተማሪዎቹ የተለያዩ ዘውግን የሚያካትቱ ምዕራፎችን የያዙ ከአንድ እስከ ሁለት የመረጃዊ መጽሐፎች ጥንቅር ያዘጋጃሉ። የጽሑፍ ትኩረት እንደ አሜሪካ ቅኝ ግዛቶች ያሉ ማህበራዊ ጥናቶች ውስጥ ካሉት የጥናት ርዕስ የመጣ ነው። ተማሪዎች መጽሐፋቸዉን (መጽሐፍቶቻቸዉን) ለማዘጋጀት/ለመፍጠር በሦስቱም የጽሑፍ ዓይነቶች ውስጥ የቀድሞ ትምህርት እና ችሎታን ይጠቀማሉ። የመጽሐፋቸዉን/መጽሐፍቶቻቸዉን ቅርጸት ለመግለጽ የተወሰኑ የጽሑፍ መዋቅሮችን በመጠቀም እና በማቀድ ይጀምራሉ። በተጨማሪም ውጤታማ የፅሁፍ ቴክኒኮችን ለመተንተን በተማሪ እና በታተሙ የአማካሪ ጽሑፎችን ይጠቀማሉ። ዩኒቱ/ክፍሉ የሚያበቃው በሥራቸው የህትመት በአል ነዉ። |

© 2019 ፈጣንና የዳበረ ትምህርት